# Job

## Chapter 2

### Amharic Interlinear

Reference: Amharic Selassie Bible

1

| | | |
|---|---|---|
| וַיְהִ֗י | -እና-ሆነ | H1961 |
| הַיּ֗וֹם | -ያ-ቀን | H3117 |
| וַיָּבֹ֙אוּ֙ | -እና-መጡ | H0935 |
| בְּנֵ֣י | ልጆች | |
| הָֽאֱלֹהִ֔ים | -ያ-አምላክ | H0430 |
| לְהִתְיַצֵּ֖ב | -ለ-መቆም | H3320 |
| עַל־ | -በ | |
| יְהוָ֑ה | እግዚአብሔር | H3068 |
| וַיָּב֤וֹא | -እና-መጣ | H0935 |
| גַֽם־ | ደግሞ | H1571 |
| הַשָּׂטָן֙ | -ያ-ሰይጣን | H7854 |
| בְּתֹכָ֔ם | -በ-መካከላቸው | H8432 |
| לְהִתְיַצֵּ֖ב | -ለ-መቆም | H3320 |
| עַל־ | -በ | |
| יְהוָֽה׃ | እግዚአብሔር | H3068 |

ከዕለታት አንድ ቀን እንዲህ ሆነ፤ የአምላክ ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም መጡ፥ ሰይጣን ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም በመካከላቸው መጣ።

2

| | | |
|---|---|---|
| וַיֹּ֤אמֶר | -እና-አለ | H0559 |
| יְהוָה֙ | እግዚአብሔር | H3068 |
| אֶל־ | -ወደ | H0413 |
| הַשָּׂטָ֔ן | -ያ-ሰይጣን | H7854 |
| אֵ֥י | ከየት | H0335 |
| מִזֶּ֖ה | -ከ-ይህ | H2088 |
| תָּבֹ֑א | ትመጣለህ | H0935 |
| וַיַּ֨עַן | -እና-መለሰ | |
| הַשָּׂטָ֤ן | -ያ-ሰይጣን | H7854 |
| אֶת־ | (ነገር) | H0853 |
| יְהוָה֙ | እግዚአብሔር | H3068 |
| וַיֹּאמַ֔ר | -እና-አለ | H0559 |
| מִשֻּׁ֣ט | -ከ-መዞር | |
| בָּאָ֔רֶץ | -በ-ምድር | H0776 |
| וּמֵֽהִתְהַלֵּ֖ךְ | -እና-ከ-መሄድ | H1980 |
| בָּֽהּ׃ | -በ-እርሷ | |

እግዚአብሔርም ሰይጣንን። ከወዴት መጣህ? አለው። ሰይጣንም። በምድር ላይ ዞርሁ፥ በእርስዋም ተመላለስሁ ብሎ ለእግዚአብሔር መለሰ።

3

| | | |
|---|---|---|
| וַיֹּ֨אמֶר | -እና-አለ | H0559 |
| יְהוָ֜ה | እግዚአብሔር | H3068 |
| אֶל־ | -ወደ | H0413 |
| הַשָּׂטָ֗ן | -ያ-ሰይጣን | H7854 |
| הֲשַׂ֣מְתָּ | አስተዋልክ-ን | |
| לִבְּךָ֮ | ልብህ | |
| אֶל־ | -ወደ | H0413 |
| עַבְדִּ֣י | አገልጋዬ | H5650 |
| אִיּוֹב֒ | ኢዮብ | H0347 |
| כִּי֩ | ምክንያቱም | |
| אֵ֨ין | የለም | H0369 |
| כָּמֹ֜הוּ | እንደ-እርሱ | H3644 |
| בָּאָ֗רֶץ | -በ-ምድር | H0776 |
| אִ֣ישׁ | ሰው | H0376 |
| תָּ֧ם | ፍጹም | H8535 |
| וְיָשָׁ֛ר | -እና-ቅን | H3477 |
| יְרֵ֥א | ፈሪ | H3373 |
| אֱלֹהִ֖ים | አምላክ | H0430 |
| וְסָ֣ר | -እና-የራቀ | H5493 |
| מֵרָ֑ע | -ከ-ክፋት | |
| וְעֹדֶ֙נּוּ֙ | -እና-ገና | H5750 |
| מַחֲזִ֣יק | የጸና | H2388 |
| בְּתֻמָּת֔וֹ | -በ-ፍጹምነቱ | H8538 |
| וַתְּסִיתֵ֥נִי | -እና-አነሳሳሽኝ | H5496 |
| ב֖וֹ | -በ-እርሱ | |
| לְבַלְּע֥וֹ | -ለ-ማጥፋት | H1104 |
| חִנָּֽם׃ | ያለ-ምክንያት | H2600 |

እግዚአብሔርም ሰይጣንን። በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም፤ በከንቱም አጠፋው ዘንድ አንተ በእርሱ ላይ ምንም ብታንቀሳቅሰኝ፥ እስከ አሁን ፍጹምነቱን ይዞአል።

4

| | | |
|---|---|---|
| וַיַּ֧עַן | -እና-መለሰ | |
| הַשָּׂטָ֛ן | -ያ-ሰይጣን | H7854 |
| אֶת־ | (ነገር) | H0853 |
| יְהוָ֖ה | እግዚአብሔር | H3068 |
| וַיֹּאמַ֑ר | -እና-አለ | H0559 |
| ע֣וֹר | ቆዳ | H5785 |
| בְּעַד־ | -በ-ዙሪያ | H1157 |
| ע֗וֹר | ቆዳ | H5785 |
| וְכֹל֙ | -እና-ሁሉ | H3605 |
| אֲשֶׁ֣ר | የ | |
| לָאִ֔ישׁ | -ለ-ሰው | H0376 |
| יִ֖תֵּן | ይሰጣል | H5414 |
| בְּעַ֥ד | -በ-ዙሪያ | H1157 |
| נַפְשֽׁוֹ׃ | ነፍሱ | H5315 |

ሰይጣንም መልሶ እግዚአብሔርን። ቁርበት ስለ ቁርበት ነው፤ ሰው ያለውን ሁሉ ስለ ሕይወቱ ይሰጣል።

5

| | | |
|---|---|---|
| אוּלָם֙ | ግን | H0199 |
| שְֽׁלַֽח־ | ልክ | H7971 |
| נָ֣א | እባክህ | H4994 |
| יָֽדְךָ֔ | እጅህ | H3027 |
| וְגַ֥ע | -እና-ንካ | H5060 |
| אֶל־ | -ወደ | H0413 |
| עַצְמ֖וֹ | አጥንቱ | H6106 |
| וְאֶל־ | -እና-ወደ | H0413 |
| בְּשָׂר֑וֹ | ሥጋው | H1320 |
| אִם־ | ቢሆን | |
| לֹ֥א | አይ | H3808 |
| אֶל־ | -ወደ | H0413 |
| פָּנֶ֖יךָ | ፊትህ | H6440 |
| יְבָרֲכֶֽךָּ׃ | ይረግምሃል | H1288 |

ነገር ግን አሁን እጅህን ዘርግተህ አጥንቱንና ሥጋውን ዳብስ፤ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል አለው።

6

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וַיֹּ֣אמֶר | יְהוָ֣ה | אֶל־ | הַשָּׂטָ֑ן | הִנּ֥וֹ | בְיָדֶ֑ךָ | אַ֖ךְ | אֶֽת־ | נַפְשׁ֥וֹ | שְׁמֹֽר׃ |
| -እና-አለ | እግዚአብሔር | -ወደ | -ያ-ሰይጣን | እነሆ | -በ-እጅህ | ብቻ | (ነገር) | ነፍሱ | ጠብቅ |
| H0559 | H3068 | H0413 | H7854 | H2009 | H3027 | H0389 | H0853 | H5315 | H8104 |

እግዚአብሔርም ሰይጣንን። ሕይወቱን ተወው እንጂ እነሆ፥ እርሱ በእጅህ ነው አለው።

7

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וַיֵּצֵא֙ | הַשָּׂטָ֔ן | מֵאֵ֖ת | פְּנֵ֣י | יְהוָ֑ה | וַיַּ֤ךְ | אֶת־ | אִיּוֹב֙ | בִּשְׁחִ֣ין | רָ֔ע | מִכַּ֥ף | רַגְל֖וֹ | [עד] | )וְעַ֥ד( | קָדְקֳדֽוֹ׃ |
| -እና-ወጣ | -ያ-ሰይጣን | -ከ-ዘንድ | ፊት | እግዚአብሔር | -እና-መታ | (ነገር) | ኢዮብ | -በ-ቁስል | ክፉ | -ከ-መዳፍ | እግሩ | (እስከ) | -እና-እስከ | ራስ-ቅሉ |
| H3318 | H7854 | H0854 | H6440 | H3068 | H5221 | H0853 | H0347 | H7822 | | H3709 | H7272 | H5704 | H5704 | H6936 |

ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፥ ኢዮብንም ከእግሩ ጫማ ጀምሮ እስከ አናቱ ድረስ በክፉ ቍስል መታው።

8

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וַיִּקַּח־ | ל֣וֹ | חֶ֔רֶשׂ | לְהִתְגָּרֵ֖ד | בּ֑וֹ | וְה֖וּא | יֹשֵׁ֥ב | בְּתוֹךְ־ | הָאֵֽפֶר׃ |
| -እና-ወሰደ | -ለ-እርሱ | ሸክላ | -ለ-መፋቅ | -በ-እርሱ | -እና-እርሱ | ተቀመጠ | -በ-መካከል | -ያ-አመድ |
| H3947 | | H2789 | H1623 | | H1931 | H3427 | H8432 | H0665 |

ሥጋውንም ይፍቅበት ዘንድ ገል ወሰደ፥ በአመድም ላይ ተቀመጠ።

9

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וַתֹּ֤אמֶר | לוֹ֙ | אִשְׁתּ֔וֹ | עֹדְךָ֖ | מַחֲזִ֣יק | בְּתֻמָּתֶ֑ךָ | בָּרֵ֥ךְ | אֱלֹהִ֖ים | וָמֻֽת׃ |
| -እና-አለች | -ለ-እርሱ | ሚስቱ | ገና-ህ | የጸና | -በ-ፍጹምነትህ | ርገም | አምላክ | -እና-ሙት |
| H0559 | | H0802 | H5750 | H2388 | H8538 | H1288 | H0430 | H4191 |

ሚስቱም። እስከ አሁን ፍጹምነትህን ይዞሃልን? እግዚአብሔርን ስደብና ሙት አለችው። (የሚቀጥለው ከግሪክ የተጨመረ ነው) ዳግመኛ እግዚአብሔርን
ጥቂት ወራት ደጅ እጠናዋለሁ፤ ዳግመኛም መከራውን እታገሠዋለሁ፥ የቀድሞ ኑሮዬንም ተስፋ አደርገዋለሁ ትላለህን? አለችው። እንደዚህሳ እንዳትል ከዚህ
ዓለም እነሆ ስም አጠራርህ ጠፋ፤ ሴቶች ልጆቼና ወንዶች ልጆቼም ሞቱ እኔስ ዘጠኝ ወር ሳረግዝ ሳምጥ ስወልድ ሳይረቡኝ ሳይጠቅሙኝ በከንቱ ደከምሁ
አለች። አንተም በመግል ተውጠህ በትል ተከብበህ ትኖራለህ፤ ሌሊቱን ሁሉ ስትዘብር ታድራለህ። እኔ ግን እየዞርሁ እቀላውጣለሁ። ከአንዱ አገር ወደ አንዱ
አገር ከአንዱ ቤት ወደ አንዱ ቤት እሄዳለሁ፤ ከድካሜ በእኔ ላይ ካለ ከችግሬም እርፍ ዘንድ ከጧት ጀምሮ ፀሐይ እስኪገባ ድረስ እጠብቃለሁ፤ አሁን ግን
እግዚአብሔርን የማይገባ ቃል ተናገርኸው ሙት አለች።

10

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וַיֹּ֣אמֶר | אֵלֶ֗יהָ | כְּדַבֵּ֞ר | אַחַ֤ת | הַנְּבָלוֹת֙ | תְּדַבֵּ֔רִי | גַּ֣ם | אֶת־ | הַטּ֗וֹב | נְקַבֵּל֙ | מֵאֵ֣ת |
| -እና-አለ | -ወደ-እርሷ | -እንደ-መናገር | አንድ | -ያ-ሞኞች | ትናገሪያለሽ | ደግሞ | (ነገር) | -ያ-ጥሩ | እንቀበል | -ከ-ዘንድ |
| H0559 | H0413 | H1696 | H0259 | H5036 | H1696 | H1571 | H0853 | | H6901 | H0854 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| הָאֱלֹהִ֔ים | וְאֶת־ | הָרָ֖ע | לֹ֣א | נְקַבֵּ֑ל | בְּכָל־ | זֹ֛את | לֹא־ | חָטָ֥א | אִיּ֖וֹב | בִּשְׂפָתָֽיו׃ |
| -ያ-አምላክ | -እና-(ነገር) | -ያ-ክፉ | አል | እንቀበል | -በ-ሁሉ | ይህ | አል | ኃጢአት-ሠራ | ኢዮብ | -በ-ከንፈሮቹ |
| H0430 | H0853 | | H3808 | H6901 | H3605 | H2063 | H3808 | H2398 | H0347 | H8193 |

פ
፤

እርሱ ግን አንቺ ከሰነፎች ሴቶች እንደ አንዲቱ ተናገርሽ፤ ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን፥ ክፉ ነገርንስ አንቀበልምን? አላት። በዚህ ሁሉ ኢዮብ
በከንፈሩ አልበደለም።

11

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וַיִּשְׁמְע֞וּ | שְׁל֣שֶׁת ׀ | רֵעֵ֣י | אִיּ֗וֹב | אֵ֣ת | כָּל־ | הָרָעָ֣ה | הַזֹּאת֮ | הַבָּ֣אָה | עָלָיו֒ | וַיָּבֹ֙אוּ֙ |
| -እና-ሰሙ | ሦስት | ወዳጆች | ኢዮብ | (ነገር) | ሁሉ | -ያ-ክፋት | -ያ-ይህች | -ያ-የመጣች | -በ-እርሱ | -እና-መጡ |
| H8085 | H7969 | H7453 | H0347 | H0853 | H3605 | | H2063 | H0935 | | H0935 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| אִ֣ישׁ | מִמְּקֹמ֔וֹ | אֱלִיפַ֣ז | הַתֵּימָנִ֗י | וּבִלְדַּ֤ד | הַשּׁוּחִי֙ | וְצוֹפַ֣ר | הַנַּעֲמָתִ֔י | וַיִּוָּעֲד֣וּ | יַחְדָּ֔ו |
| ሰው | -ከ-ቦታው | ኤሊፋዝ | -ያ-ቴማናዊ | -እና-ቢልዳድ | -ያ-ሹሓዊ | -እና-ጾፋር | -ያ-ናዕማታዊ | -እና-ተቀጣጠሩ | አብረው |
| H0376 | H4725 | H0464 | H8489 | H1085 | H7747 | H6691 | H5284 | H3259 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| לָב֛וֹא | לָנֽוּד־ | ל֖וֹ | וּֽלְנַחֲמֽוֹ׃ |
| -ለ-መምጣት | -ለ-ማጽናናት | -ለ-እርሱ | -እና-ለ-ማጽናናት |
| H0935 | H5110 | | H5162 |

ሦስቱም የኢዮብ ወዳጆች ይህን የደረሰበትን ክፉ ነገር ሁሉ ሰምተው ከየአገራቸው መጡ፤ እነርሱም ቴማናዊው ኤልፋዝ፥ ሹሐዊው በልዳዶስ፥ ነዕማታዊው
ሶፋር ነበሩ። እነርሱም ሊያዝኑለትና ሊያጽናኑት በአንድነት ወደ እርሱ ለመምጣት ተስማሙ።

12

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וַיִּשְׂאוּ | אֶת־ | עֵינֵיהֶם | מֵרָחוֹק | וְלֹא | הִכִּירֻהוּ | וַיִּשְׂאוּ | קוֹלָם | וַיִּבְכּוּ | וַיִּקְרְעוּ |
| -እና-አነሱ | (ነገር) | ዓይኖቻቸው | -ከ-ርቀት | -እና-አል | አወቁት | -እና-አነሱ | ድምፃቸው | -እና-አለቀሱ | -እና-ቀደዱ |
| H5375 | H0853 | | H7350 | H3808 | | H5375 | | H1058 | H7167 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| אִישׁ | מְעִלוֹ | וַיִּזְרְקוּ | עָפָר | עַל־ | רָאשֵׁיהֶם | הַשָּׁמָיְמָה׃ |
| ሰው | ልብሱ | -እና-ወረወሩ | አፈር | -በ | ራሶቻቸው | -ያ-ሰማያት-ወደ |
| H0376 | H4598 | H2236 | H6083 | | | H8064 |

ከሩቅም ሆነው ዓይናቸውን ባነሡ ጊዜ አላወቁትም፤ ድምፃቸውንም አሰምተው አለቀሱ፤ እያንዳንዳቸውም መጐናጸፊያቸውን ቀደዱ፥ ወደ ላይም ወደ ራሳቸው ላይ ትቢያ ነሰነሱ።

13

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| וַיֵּשְׁבוּ | אִתּוֹ | לָאָרֶץ | שִׁבְעַת | יָמִים | וְשִׁבְעַת | לֵילוֹת | וְאֵין־ | דֹּבֵר | אֵלָיו |
| -እና-ተቀመጡ | ከ-እርሱ-ጋር | -ለ-ምድር | ሰባት | ቀናት | -እና-ሰባት | ሌሊቶች | -እና-የለም | ተናጋሪ | -ወደ-እርሱ |
| H3427 | H0854 | H0776 | H7651 | H3117 | H7651 | H3915 | H0369 | H1696 | H0413 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| דָּבָר | כִּי | רָאוּ | כִּי־ | גָדַל | הַכְּאֵב | מְאֹד׃ |
| ቃል | ምክንያቱም | አዩ | ምክንያቱም | ታላቅ | -ያ-ሥቃይ | እጅግ |
| H1697 | | H7200 | | H1431 | H3511 | H3966 |

ሰባት ቀንና ሰባት ሌሊትም ከእርሱ ጋር በምድር ላይ ተቀመጡ፤ ሕመሙም እጅግ እንደ በዛ አይተዋልና ከእነርሱ አንድ ቃል የሚናገረው አልነበረም።